# ኑሩልኝ!

አፈር ነህና ወዳፈር
ትመለሳለህ መባሉ
አዲስ አይደለም ለሰሚው
ሃቅ ነውና ብሂሉ።
ይህ አይደለም ምስጢሩ
የሕይወት እንቆቅልሹ
እየኖሩ መሞት እንጂ
አለመሞት፥ ሞትን ሲሹ።
ምስጢሩ እዚያ ላይ ነው
ሞተዋል ሲባል መኖሩ
በቁመና ተቀብሮ
አለመሞትን ማስመስከሩ።
ከሞቱት በላይ ቆሞ
ከቆሙት በታች ተቀብሮ
በህልውና እየሞቱ
እየተቀበሩ ኑሮ
ይህ ነው የሕይወት እንቆቅልሽ
ድብቁ ምስጢር ከባዱ
በቁም ተቀብሮ እየኖሩ
ኑሮን ካለመኖር ማዋሃዱ
ሕይወትን እየሞቱ
ሞትን ከመኖር ማዋደዱ።
እንደሌሉ ተቆጥሮ
በሞትም ላይ ፊትን ማዞር
ጥልቁ ምስጢር እዚያ ላይ ነው
እየኖሩ አለመኖር።
ግን . . . ማን ያውቃል?
የዛሬ መዋረዳቸው
ለነገ ቢሆንስ ክብራቸው?
ምናልባትም . . . ለምድሪቱ ሲቀርቡ
ከትቢያዋ ሲልሱ
ይለመልም ይሆን ተስፋ
ከአፈርዋ ሲቁዋደሱ?
እየኖሩ እንደሌሉ
እየሞቱ እንደኖሩ
ፍትህን እንደተጠሙ
ፍቅርን እንደተራቡ
እየታዘቡ . . .
እየሞቱ ይኖራሉ
እየጫጩ ያድጋሉ
አዎ . . . ቅራኔው እዚህ ላይ ነው
ማህበረሰባዊ ምጸቱ
የመኖራቸውን አለመኖር
በዝምታ መመልከቱ።
ግን . . . ማን ያውቃል?
ዓለም ብትዘነጋቸውም
የደላው ቢጠየፋቸውም
የሞላለት ቢንቃቸውም
እያየ ባያያቸውም . . .
ይሆኑ ይሆናል አንድ ቀን
የወገን ቤዛ አለኝታ
ለኢትዮጵያም አዲስ ተስፋ
መድኃኒትና መከታ።

ቀምሰዋልና አፈርዋን
ልሰዋልና ትቢያዋን
ሳይሞቱ ተቀብረውባት
          ዳስሰዋልና ማህጸንዋን . . .
ማን ያውቃል?
ከሰው በላይ ሰው፥ ይሆኑ ይሆናል
ማን ያውቃል?

---

እየኖሩ እንዳይኖሩ ለተደረጉት፥ ለእነቢቢሲ «ዜና» ለሆኑት ያገሬ ልጆች በሙሉ
ቴዎድሮስ አበበ
June 27, 2006